# መደመር ከስባት ወር በኋላ !!

በ መጋቢት 25/ 2010 ዓ. ም. ዶክተር ዓቢይ አሕመድ መደመር የሚለውን መሪ ቃል ተናገሩ። በዚያን ዕለት፣ አገሪቱ ያለችበትን አደጋኛ የሆነ ሁኔታ ያልገባቸው ጥቂት ቡድኖችና ግለሰቦች በስተቀር፣ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ፣ ገና ማለዳ ፀሃይ አድማሱን ሰንጥቃ ስትወጣ በፍጥረታት ሁሉ የምትፈጥረውን ዐይነት የደስታ ስሜት አሰፈነበት። ንግግሩ የፈጠረው ደስታና ብሩሕ ተስፋ ገደብ አልነበረውም። መንፈሱ በደስታ ተሞላ፣ እስከዚያን ወቅት ድረስ አገራችን ልክ እንደ ዩጎዝላቪያ ልትበታተን ነው የሚል ስጋት ተጭኖት የነበረው ዜጋ ሁሉ ያ የጭንቀት መንፈስ ተገፈፈለት።

ከዚያ ታሪካዊ ንግግር ቀጥለው ባሉት ቀናትና ሳምንታት፣ ባገሪቱ ታላላቅ ከተማዎች ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ድጋፉንና ደስታውን ገለጸ። ያ ታሪካዊው አረንጓዴ ብጫ ቀይ ባንዴራም አገሪቷን በሙሉ አጥለቀለቃት። በዓፄው ጊዜ በነበረው አንጻራዊ የሰላም ጊዜ እንኳን ይህን ያህል ባንዴራ ታይቶ አያውቅም። ህዝቡ ይህ ነው የማይባል እፎይታ ተሰማው። ይህ ነው ለውጥ ማለት።

ከትንሽ ጊዜ መረጋጋትና ለውጡ ያስከተለው ከፍተኛ የመመርቀን ደስታ መስከን በኋላ ቆም ብሎ ሁኔታውን መገምገም አስፈላጊ ነው። ይህ ለውጥ ቀጣይ ነው ወይ? አስተማማኝስ ነው ወይ? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። የመጠየቁ መንፈስ፣ ለመቃረን ሳይሆን፣ ከመደሰቱና ከተፈጠረው ተስፋ ጋር በተያያዘ ነው። ቀጣይነቱና አስተማማኝነቱን እንድንጠይቅ የሚያደርገንም፣ ይህ የመጣው ለውጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለረዥም ጊዜ የታገለለትና ሲመኘው የነበር ጉዳይ ስለነበረ ነው። ስለሆነም ይህ ለውጥ አስተማማኝ መሠረት ጥሏል ወይ? ወይንስ ገና እግር ያልተከለ፣ ሰንደልደል የሚል በቀላሉ ሊቀለበስ የሚችል ነው ለሚሉ ተገቢ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ነው።

ለውጡን ተከትሎ በርካታ በደርግ ብሎም በወያኔ/ኢህአዴግ ይሳደዱ የነበሩና እንደ ጠላት ተፈርጀው በስደት የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ቀደም ብለው ይዘዉት የነበረውን "ሁለ ገብ" እና "የትጥቅ ትግል" የትግል ስልታቸውን እርግፍ አድርገው በመተው፣ የዚህ ለውጥ አካል በመሆን ለሃገራችንና እና ለህዝባችን ተስፋ ያለው መጻኢ እድል የበኩላችንን ሚና መጫወት አለብን በማለት ጠቅልለው ወደ አገር ቤት የገቡበት ወቅት ነው። ይህ እርምጃ ሁለት ሶስት ነገሮችን በግልጽ ያስቀምጣል። በቅድሚያ አዲስ ለመጣው አመራር በቃሉና ባንዳንድ ተግባሩ ሙሉ አመኔታ መስጠት ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ወደናፈቁት አገራቸው መግባትና በሕዝባቸው መሃል ሆነው ዓላማቸውን ግብ ለማድረስ ያላቸውን ከፍተኛ ጉጉት ያሳያል።

ይህ ግኝት/ለውጥ ሁሉም ዜጋ እኩል ለሚሆንባት፣ የህግ የበላይነት ለሚሰፍንባት፣ የሕዝቧ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነቷ ለሚከበርባት አዲስቷ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ፈር ቀዳጅ ነው። ባገሩ ውስጥና እንዲሁም በውጭ አገር የሚኖረው የዲያስፖራው ክፍልም በደስታ ተቀበሎታል። ያ ምን አገር አለኝ፣ ምን መሪስ ኑሮኝ ያውቃል በሚል ቀቢጸ ተስፋ መንፈስ ተወጦ የነበረው ሁሉ አሁን ገና የኔ መንግስት፣ የኔ የምለው መሪ አገኘሁ በሚል ብሩሕ ተስፋ ተሞላ።

ከላይ የተጠቀሰው የፓርቲ/ፈንጠዚያ የምርቃና ጊዜ አለፈ። መንፈሱ ወደ እውነተኛ ያገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ተመለሰ። ለውጡ እውን መሆኑ ባይሳትም፣ የተገኘው ለውጥ ግን በቋሚነት ቀጣይ ሊሆን እንደሚችል ምንም አስተማማኝ ነገር ማየት አልተቻለም። ሆኖም ግን ይህን ግንዛቤ ይዞ ለውጡን ማስቀጠል አለብን፣ ከመቀልበስ ማዳን አለብን የሚል ጠንካራ መንፈስ ተፈጠረ። ለዚህ ለውጥ ዘብ መቆም አለብን የሚል ሃሳብም ተጠናክሮ ወጣ። ይህ ግን ምን ማለት ነው? ተግባራዊነቱስ በምን ይገለጻል?

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ለውጡን የኔ ብለው የተቀበሉና ለውጡ ተጠናክሮ የተደላደለ መሰረት እንዲይዝ የሚፈልጉ ሃይሎች በመሃላቸው መተማመን እንዲኖር ያስፈልጋል። በነዚህ ኃይሎች መሃል ምንም ዓይነት ነፋስ መግባት የለበትም።

የፋሽሽታዊ ደርግና የኢዴሞክራሲያዊና ጎጠኛ ወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዞችን ለመቋቋምና ለማስወገድ በተደረገው ትግል ወቅት የተፈጠሩ ቅራኔዎችና መፋተጎች አሁንም አሉ። መፍትሄ ስይገኝላቸው እንዲሁ ተዳፍነው ያሉና አመቺ ሁኔታ ሲፈጠርላቸው ፈንድተው ለውጡን ሊያዳክሙ ብለውም ሊቀለብሱ ይችላሉ።

ከደርግና ወያኔ ኃይሎች ውጭ በሆኑ ድርጅቶች መሃል

1. ደርግንና ወያኔን ለመቋቋም በተደረጉት ትግሎች ወቅት፣ ተቃዋሚ ኃይሎች በመሃላቸው የነበሩ ልዩነቶችን በሰላማዊ መልክ ማስወገድ ባለመቻላቸው ወደ ተካረረ ቅራኔ ገብተው ወደ ጦርነት በማምራት ደም ተቃብተዋል። ቂም በቀሉ አሁን ድረስ አለ። ይህ መፈወስ የሚያስፈልገው የራሱ የሆነ ጠባሳ ጥሎ አልፏል
2. በያንዳንዱ ድርጀት ውስጥ የውስጠ-ፓርቲ ትግል ሲከሰት፣ ልዩነቱን ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍታት ባለመቻልና እንዲሁም ባነስተኛ ደረጃ የነበረን የልዩነት ነጥብ በማጥበብ የድርጅቱን አንድነት ይዘው መቀጠል ስላልቻሉ ልዩነቱ ወደ መካረር በመሄድ ቅራኔው ተባብሶ ወደ በትጥቅ እስከ መፋለም ደርሶ መቆሳሰልና መዳማት ላይ ተደርሷል።

ይህ ተቃዋሚ በሚባሉ ኃይሎች ውስጥ የተፈጠረው የመቃቃርና የመዳማት ስሜቱ አሁን ድረስ ያለ ነው። አሁን በዶክተር ዓብይ መንግሥት የሰላም ጥሪ መሰረት ከውስጥም ከውጭም ወደ ሰላማዊ ትግሉ የተመለሱ በርካታ ድርጅቶችና ታጣቂዎች እንዲሁም ሕዝባዊ ድርጅቶችና ግለሰቦች ይህን የቂም መንፈስ ሳያርቁ የ "ተደመሩ" ናቸው። እንዲህም ስለሆነ በመሃላቸው የነበሩት የተለያዩ ቅራኔዎች አገርሽተው ለውጡን አደጋ ላይ ሊጥሉ እንደሚችሉ ላንዴም ቢሆን መዘንጋት የለብንም። የዚህን ስጋት ሁኔታ ቁልጭ ባለ መልክ በተጨባጭ ለማሳየት ወደ ኋላ ብዙ ሳንሄድ የቅርቡን እንኳን ብናይ ቅራኔዎች አገርሽተው ይህ በመላ ህዝባችን ውስጥ ተስፋን ያጫረ ለውጥ የመቀልበስ አደጋ እያንዣበበት እንዳለ የሚያመላክቱ ሁኔታዎችን እንይ።

- የወያኔ በመቀሌ፣ ብሎም በጠቅላላ ትግራይ ውስጥ ከትሞ፣ መሽጎ ነጻነት ሳያውጅ ሆኖም ግን ከማእከላዊው መንግስት ውጭ በመሆን ራሱን በማስተዳደር ላይ መሆኑ
- የኦነግ ትጥቅ እፈታለሁ አልፈታም ግርግርና እሱ የፈጠረው አስደንጋጭ ሁኔታ
- በምስራቅ ኢትዮጵያ በሶማሊ ኢትዮጵያውያንና ኦሮሞዎች መሃከል ይተፈጠረው ግጭትና መፈናቀል፤ በአዲስ አበባ አካባቢ በቡራዩ የተከሰተው አሰቃቂ ግድያና መፈናቀል፤ በራያ፣ ወልቃይት ጠገዴና ጸለምት በማንዣበብ ላይ ያለው በጣም አስፈሪ ሁኔታዎች
- በዓለም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የታጠቀ ጦር ሰተት ብሎ ቤተመንግሥት በመግባት ያለ ቀጠሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በማነጋገር ፑሽ አፕ ማሰራት
- የፌደራል መንግሥቱ መቀመጫ፣ ያገሪቱና የመላ አፍሪካ መዲና የሆነችውን አዲስ አበባን የኦሮሞ ብቻ ነች ቅብርጥሴ በማለት ለቅርጫ ማቅረብ

ለነዚህ ችግሮች፣ መንግሥትና የፖለቲካ ድርጅቶች (መንግሥት ተፎካካሪ የሚላቸው) አንዱ ሌላውን ሳያገል፣ በመገናኘትና በመምከር መፍትሄ ካልተገኘላቸው ያለ ምንም ጥርጥር ለውጥ ቀልባሽ እንደሚሆኑ ግልጽ ነው።

ሁለተኛ ጉዳይ ደግሞ፣ ከላይ ከተጠቀሰው ሌላ፣ በገዥው ፓርቲ በኩልስ ይህን አወንታዊ ለውጥ አጠናክሮ፣ እንዳይቀለበስ ለማድረግ በሚደረገው ሂደት ምን ዓይነት ተግዳራቶች በውስጡና ከፊቱ ተደቅነዋል። ይህ ለውጥ እውን እንዲሆንና በቋሚነት እንዲቀጥል ለማድረግ አንዳንድ መሰረታዊ የሆኑ ለውጦች ያስፈልጋሉ።

በወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት ወቅት የነበሩ አንዳንድ መዋቅሮች፣ አሰራሮችና ሕጎች መቀየር ይኖርባቸዋል። በምሳሌነት ደረጃ ሊጠቀሱ ከሚችሉት አንዳንዶቹ

2.i. የምርጫ ቦርድ አመሰራረትና አካሄድ
2.ii. በወያኔ ብቸኛ አባላት ተይዘው የነበሩ የስለላና የጸጥታ ድርጅቶች
2.iii. ሚዲያንና፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችን ቀፍድደው በመያዝ አላፈናፍን ያሉ ሕግጋት
2.iv. ገደብ ያጣ፣ በቡድንና በግለሰብ ደረጃ እየተፈጸሙ ያሉ ያገር ሃብት ዝርፊያዎችና ሙስናዎች
2.v. በስመ የብሔር ብሔረሰብ መብት ማስጠበቅ፣ በታሪካዊ ሂደት ተሳስሮ ለአማኢት ዓመታት በፍቅርና በሰላም የኖረን ሕዝብ በማበጣበጥ የኢትዮጵያዊነት/አንድነት መንፈስን ማኮሰስና ማኮላሸት ይገኙበታል።

ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች የተሟሉና ሁሉን የዘረዘሩ አይደሉም። እነዚህ በዋናነትና በምሳሌነት የተነሱ እንጂ። ችግሩ እንዚህን ግድፈቶች የፈጠሩት ሕጎችና አሰራሮች አሁን ድረስ በሕግ መጽሓፍ ውስጥ እንዳሉ ናቸው። ዶክተር ዓቢይና ጓዶቹ በሆነ ሰበብ/ምክንያት ዘወር ካሉ፣ እኒህ አሁንም በመጽሓፍ ውስጥ ያሉ፣ ያልተነሱና ያልተቀየሩ ሕጎች መልሰህ ተግባራዊ ማድረግ ቀላል ነው። ተመልሰህ ወደነበርክበት አዘቅት ውስጥ መግባት ማለት ነው። ተስፋ የተደረገበት ለውጥ ተነነ ማለት ነው።

ይህ ሲባል ግን፣ ምንም ለውጥ አልመጣም ማለት አይደለም። በዶክተር ዓብይ የሚመራው መንግሥት በርካታ፣ ለውጥን የሚያቀነቅኑ ተግባራት እየፈጸመ ነው። በማስረጃነት ለመጥቀስ ያህል ፦

i. ሙሉ በሙሉ እንኳን ባይሆንም (በትግራይ ወስጥ ለዓመታት በጉድጓድ ውስጥ የታሸጉ እስረኞችን አይመለከትም) በርካታ የፖለቲካ እስረኞች ተፈተዋል።
ii. የሃገሪቱን የጦር ኃይሎች እንደ መዥገር ሙጭጭ ብለው ይቆጣጠሩት የነበሩ የተወሰኑ (የድሮዉን ጠቅላይ ኤታ ማጀሩን ጨምሮ) የወያኔ ጀነራሎችን በማንሳት ሰራዊቱ መጠነኛ ዴሞክራሲያዊ አየር እንዲተነፍስ አድርጎል።
iii. ደርግም ይሁን ወያኔ ለረዥም ጊዜ በጠላትነት ፈርጀው አገራዊ ስሜቱን አደብዝዘውበት የነበረውን፣ ለዓመታት በስደት የተቀመጠውን ኢትዮጵያዊ ዲያስፖራ፣ ዶክተር ዓብይ ስራዬ ብሎ ሄዶ በየከተማው እየዞረ የለውጥ ሂደቱን በማብሰር ኢትዮጵያዊነትን መልሶ እንዲላበስ አድርጓል
iv. የስምምነት ነጥቦቹ ይፋ ባይሆኑምና ባንዳንድ አካባቢዎች ልዩ ጥርጣሬን ቢፈጥሩም፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረውን የጦርነት መንፈስ አስወግዶ ሕዝብ ለሕዝብ ግኑኝነትን ፈጥሯል
v. ከውጭ መንግስታት ጋር ግኑኝነት በመፍጠር ላገሪቱ ጠቀሜታ ያላቸው ሁኔታዎችን ፈጥሯል። ይህ ጉዳይም ልክ እንደ የኤርትራው ጉዳይ የስምምነት ነጥቦቹ ይፋ ስላልሆኑ ጥርጣሬ ውስጥ ገብቷል።

አሁን አገሪቱ ያለችበት ሁኔታ ይህን ይመስላል። አወንታዊና አሉታዊ ጎኖች አሉት። መታየት ያለበት ጉዳይ፣ የተካሄደው ለውጥ አስፈላጊና መደረግ የነበረበት ነው። በሌላ በኩል ለውጡ አሁንም ገና በእንጭጩ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ገና ዳዴ እያለ ነው። እንዲህም ስለሆነ ሁሉም ኃይሎች፣ መንግሥት፣ ተፎካካሪ ድርጅቶች፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ሚዲያዎች ባንድ ጎኑ ያለማወላወል ድጋፋቸውን መስጠት ሲገባቸው፣ በሌላው ጎኑ ግን ድካም ሲያዩ ወደ ኋላ ሳይሉ

ለመንግሥት ማሳየት፣ መጠቆም ይኖርባቸዋል።

ስለዚህ አሁን ያለንበት ቦታ ላይ ሆነን ቆም ብለን ስናይ የሚከተሉትን ሁኔታዎች እናያለን። መንግሥትም ሆነ ተፎካካሪ ድርጅቶች በተናጠል የትም ሊደርሱ እንደማይችሉ ያለ ምንም ጥርጣሬ መገንዘብ ይኖርባቸውል። ይህን ካልተገነዘቡ ታጥቦ ጭቃ ይሆንና ለወያኔና ሌሎች መሰል ድርጅቶች አመቺ ሁኔታ ይፈጥራ

። ይህ ላገሪቱም ሆነ ለህዝቧ ምንም ቢሆን አያመችም። ያቺ የምንፈልጋት፣ የምነመኛት የበለጸገች ሰላማዊት፣ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ህልም ሆና ትቀራለች።

ይህ እንዳይሆን የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል።

በመንግሥት በኩል፡

1. ይህን ለውጥ ወደፊት ለማራመድ መንግሥት በሚወስዳቸው እርምጃዎች አጋሮቹ የሆኑትን ተፎካካሪ ድርጅቶች ማማከርና ማሳተፍ ይኖርበታል።
2. ባጭር ጊዜ ውስጥ፣ ባለፉት 40 ዓመታት በተካሄዱ ተግባራት/ትግሎች ውስጥ የተፈጠሩትን ቅራኔዎች በውይይትና ይቅር በመባባል ኢትዮጵያዊ አንድነትን ለማጠናከር ከመንግሥትም ሆነ ከሌሎች ፖለቲካዊ ድርጅቶች ነጻ የሆነ ኮሚሽን በማቋቋም ሃገራዊ የሰላምና የእርቅ ጉባኤ መሰየም ይኖርበታል። ይህን ለማድረግና መጠራጠርን ለማስወገድ መንግሥት ተፎካካሪ ድርጅቶችን በሂደቱ ማሳተፍ ይኖርበታል።
3. መጠራጠርንና አለመተማመንን በማስቀረት ባንድ ላይ ለመጓዝ መንግሥት ከማንም ኃይልና መንግሥታት ጋር የሚያደርገውን ስምምነት ወዲያውኑ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይኖርበታል። ይህ ካልተደረገ መተማመን አይኖርም። ጥርጣሬ ሲኖር አብሮ ላንድ ዓላማ መስራት የሚባል መንፈስ አይፈጠርም።

በተፎካካሪ ድርጅቶች በኩል፡

1. ቀደም ሲል የነበራቸውን የተለያየ የትግል ስልት አስወግደው ወደ አገር ቤት የገቡበትን ቃል ጠብቀው ትግላቸውን በግልጽና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መቀጠል ይኖርባቸዋል
2. በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት በሕግ የተደነገገውን የመንግሥትነት ስልጣኑን መጋፋት የለባቸውም
3. ተፎካካሪ ድርጅቶች በመሃላቸው የሚፈጠር ምንም ዓይነት ቅራኔን በሃገሪቱ ሕግ መሰረት መፍትሄ መሻት ይኖርባቸዋል

እነዚህ ጉዳዮች ካልተሟሉ፣ መተማመና የአብሮነት ጉዞ አይኖርም ……… ሄዶ ሄዶ ወደ ልዩነቶች መፈጠር ብሎም መራራቅ ይመጣና ወደ እንካስላንትያ በመግባት መደመሩ ወደ መከፋፈል ያመራል። ይህ የተመኘነው ለውጥ ተቀልብሶ እንዳልሆነ ይሆናል።

ሩፋኤል ሰለሞን